

# ኢትዮጵያ

ሐምሌ/ነሐሴ 1ኛ ዓመት በነፃ የሚሠራጭ

**አበራሽ ወርቁ**

የባንክ ሠራተኛ ማህበር አባል የነበረችና በደርግ ከርቸሌ ውስጥ የተገደለች።


*ርእሰ አንቀጽ* ገፅ 2

ለብዥታና ለድንጋሬ ጊዜም ሆነ ቦታ አንስጣቸዉ!

*ዜና ከተባለ* ገፅ 3

*ምን ይሰማ... ኣገር* ገፅ 3



*ትላንትና* ገፅ 5

*የቦረና ነጌሌዎቹ የኢሕአፓ ወጣቶች ሕዝባዊ ገድል በጨረፍታ ቅኝት*

**ነፃ ሀሳብ** ገፅ 6

የተቀነባበረ የወያኔ ሴራ በኢሕአፓ ላይ



**ኢትዮጵያ ጋዜጣን**

*በተለያዩ ድረ ገጾች

ሀ. **Eprp.com**

ለ. **Asimba.org**

ሐ. **Debteraw.com**

ወዘተ.

*በ **Face book (ethiopianewspaper)**


## ለመለስ ሙት ዓመት በሚሊዮኖች የሚቆጠር ወጪ ተደረገ

መለስ ዜናዊ የሞተበትን አንደኛ ዓመት አስመልክቶ በሙቶ ሚሊዮን የሚቆጠር ብር በተለያዩ ሰበቦች ከህዝብ ካዝና ወጪ ተደርጎ መባከኑ ታወቀ::

በዚህም መሰረት በመላ ሀገሪቱ በእያንዳንዱ ወረዳና የዞን ከተሞች ሳይቀር የመለስን ሐውልት በግዳጅ አሰርተው እንዲያቆሙና በስሙ ፓርክ እንዲሰየምለት በተሰጠ ጥብቅ ትዕዛዝ መሰረት ከሕዝብ እና ከመንግስት ካዝና ገንዘብ ወጪ ተደርጎ እየተሰራ መሆኑን ተረጋግጧል::ለዚሁም ተብሎ የችግኝ ተከላ፣ የፓናል ውይይቶች እና ሌሎችም ሥነ ስርዓቶች መደረጋቸውንና ዋና በዓሉን ነሐሴ 14 ቀን 2005 ዓ.ም በአዲስ አበባ በታላቅ ድግስ እና በተለያዩ ዝግጅቶች ሲያከብሩ ሰንብተዋል::

የአፍሪካ ሀገራት መሪዎችን በዝግጅቱ ላይ እንዲገኙላቸው ከወራት አስቀድሞ ጥሪ ያደረጉላቸው ሲሆን፤ ጥሪ ከተደረገላቸው መሪዎች መሀከል፣ በዓለም አቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት እየታደነ ያለውና በቅርቡ በኢራት አዲሱ ፕሬዝዳንት በዓለ ሲመት ላይ ለመገኘት በመጉዋዝ ላይ እያለ ሳዑዲ የአየር ክልሏን በመከልከሏ የተመለሰው የሱዳኑ ፕሬዝዳንት ዑመር ሀሰን አልበሽር፤ የወያኔ ጥገኛ የሆነው የጅቡቲው ፕሬዝዳንት ዑመር ጌሌህ፤ በወያኔ ድጋፍ ስልጣን ላይ የሚገኘው የሱማሌው አዲሱ ፕሬዝዳንት ሀሰን ሼህ መሐመድ ብቻ የተገኙ ሲሆን፤ የተቀሩት ጥሪ የተደረገላቸው የአፍሪካ መሪዎች የወያኔ ባለስልጣናት እንዳሰቡት ሳይገኙ በመቅረታቸው ያቀዱት ፕሮፓጋንዳ ፉርሽ ሊሆንባቸው ችሎዋል::

### በየቦታው ዘረፋዎችና ግድያዎች መበራከታቸው ታወቀ

በአሁኑ ሰዓት የስራ አጥ ዜጎች ቁጥር በጣም ከፍተኛ በመሆኑና የኑሮ ውድነቱ እየከፋ በመምጣቱ፤ ባዲስ አበባ የወንጀለኞች ቁጥር እየበረከተ መምጣቱ ታወቀ:: ዜጎች የሚላስ የሚቀመስ በማጣታቸው ህይወታቸውን ለመታደግ ሲሉ ብቻ የገዛ ወገናቸውን ለመዝረፍና ለመግደል እየተገደዱ መሆኑን የጠቆሙት ጉዳዩን የሚከታተሉ ወገኖች ሁኔታው በዚሁ ከቀጠለ ወደፊት ኢትዮጵያ ከአፍሪካ በወንጀለኞች ብዛት አስከፊ ከሚባሉት ሀገራት ውስጥ ልትሆን ትችላለች ሲሉ ስጋታቸውን ይገልጻሉ::

ሰሞኑን ተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን በአዲስ አበባ በተለያዩ ክፍለ ከተሞች ተዘዋውሮ ለማረጋገጥ ባደረገው ሙከራ ከአራት በላይ ሰዎች በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ እና አቅራቢያ ተገድለው መገኘታቸውን ያረጋጠ ሲሆን የጉዳዮቹም ማንነት ለግዜው ባይታወቅም ከዝርፊያ ጋር የተያያዘ መሆኑ ታውቋል።

በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ እና በአቅራቢያቸው ተገድለው የሚገኙት ሰዎች የገንዘብ አቅም ያላቸውና ከፖለቲካ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የሌላቸው፤ ኮንዶሚኒየም ወይም ትልልቅ ቤቶች ተከራይተው የሚኖሩ መሆናቸው የተረጋገጠ ሲሆን ገዳዮቹ በየቀኑ ክትትል እና ጥናት አድርገው እንደገደሉዋቸው ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሎዋል::

### በሙስሊም ኢትዮጵያውያን ላይ ወያኔ የሚያካሂደው ዘመቻ ቀጥሏል

የኢድ አልፈጥር በዓል በስታዲየም በተከበረበት ዕለት፣ ወያኔ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ሙስሊሞችን በትንሿ ስታዲየም ውስጥ አግቶ ሲያሰቃያቸው እንደነበር የደረሰን መረጃ ያስረዳል::

በዕለቱ በስታዲየም ዙሪያ በተከሰተ ግጭት እና ግርግር ሕዝበ ሙስሊሙ ጫማውን ጥሎ የሸሸ በመሆኑ ከ5 ሺህ በላይ ጫማዎች መሰበሰባቸውና በማዘጋጃ ቤት መኪና ተጭኖ ወደ ቆሼ ተወስዶ እንዲቃጠል መደረጉን ከአይን እማኞች ለማረጋገጥ ተችሎዋል::

በመላ ሀገሪቱ የተፈጠረውን ውጥረት ለማርገብ እና የሙስሊሙን ህብረተሰብና የተቃዋሚ ፓርቲዎችን እንቅስቃሴ ለማዳከም ብሎም ለማጥፋት ሲል የወያኔ ቡድን በየከተማው ሕዝቡን ለመሰብሰብ ጥሪ ቢያደርግም ተቀባይነት አጥቶ ባዶ መቅረቱና የገዛ ካድሬዎቹን ብቻ ሰብስቦ የአቋዋም መግለጫ ለማውጣት እንደተገደደና በዚህም ላይ ከገዛ ከካድሬዎቹ ጭምር ከፍተኛ ተቃውሞ እንደደረሰበት ከተሰብሳቢዎቹ የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል::

### ሙስሊም ባለስልጣናት በደህንነት ክትትል እየተደረገባቸው መሆኑ ተጠቆመ

የወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣናት ከሙስሊሙ ሕብረተሰብ ተቃውሞ ጋር በተያያዘ የራሳቸውን ካድሬዎች እየተከታተሉና እየመነጠሩ ያሉ ሲሆን ሰሞኑን ባካሄዱት የምስጢር ስብሰባ ደግሞ ሙስሊም የሆኑና ከፍተኛ ስልጣን የተሰጣቸው ግለሰቦችንም ጭምር መከታተልና መመንጠር አስፈላጊ መሆኑን መወሰናቸው ታውቋል።

በዚህም መሰረት ሰሞኑን ከወረዳ እስከ ክፍለ ከተማ እና ዞን ድረስ ያሉ ካድሬዎችን ግምገማ በሚል ሰብስበዋቸው የነበረ ሲሆን በምስጢር ሙስሊም የሆኑና የሙስሊም ጉዋደኛ ያላቸውን ካድሬዎች ለግዜው በሚል ከስራ ገበታቸው ላይ እያሰነበቱዋቸው እንደሆነም ለጉዳዩ ቅርበት ካላቸው ሰዎች ለማወቅ ተችሏል::
ቁጥጥር እና ክትትል እንዲደረግባቸው ስማቸው ለደህንነት ክፍል ከተላለፈው ከፍተኛ የወያኔ ባለስልጣናት መሀከል የኦሮሚያ ምክትል ፕሬዝዳንትነት የተባለውና የአለማያ ከተማ ተወላጁ አብዱላዚዝ መሐመድ አንዱ ሲሆን ሌሎች ባለስልጣናትም በተመሳሳይ ሁኔታ ጥብቅ ክትትል እየተደረገባቸው መሆኑን ከደረሰን ጥቆማ ለመረዳት ችለናል::

ወደ ገጽ 6 ዞሯል







# ኢትዮጵያ

በኢሕአፓ የዲሲና አካባቢዉ ደጋፊ አካል
የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ

አድራሻ፡ 5309 Georgia Ave. NW. 2nd floor
Washington, VA. 20011
Tel: (202) 291 4217
E mail: dc.region.eprp@gmail.com

በጉዞ ወይም በእረፍት ላይ ሆነው ፍኖተ ሕብረት የኢሕአፓ ድምፅን ማዳመጥ ከፈለጉ **(484) 718-0523** በመደወል ይከታተሉ። ፕሮግራሙን በሰዓቱ መከታተል ካልቻሉ ለአንድ ሳምንት ያህል በማናቸውም ጊዜ ይህንኑ ስልክ በመደወል ማዳመጥ ይችላሉ።

## ርዕስ አንቀፅ

# ለብዥታና ለድንጋሬ ጊዜም ሆነ ቦታ አንስጣቸዉ!

ወያኔያዊዉ ጎሰኛና አምባገነናዊ አገዛዝ ልጡ ርሷል ፤ መቃብሩም ተምሷል። በአንጻሩ ደግሞ ፤በሕዝቡ ሠፊር ብሶት ሥር እየሰደደና ትግሉ እየጎመራ ነዉ ። የዚያኑ ያህልም የወያኔዉ መንግሥታዊ አፈናና ወከባ ደርቷል ። ትግሉ ይበልጥ እየከረረ በሄደ መጠን መምረሩ አያመልጡት እዉነት ነዉ ። የሀገራችንን አንድነትና ብሔራዊ ልዕልና ፤ እንዲሁም የዜጎችን እኩልነትና ክብር ፤ቢያንስ ወደ ቀድሞ ሥፍራዉ መልሶ ለማቆም የሚደረገዉ ትንቅንቅ በስንተኛዉ ሰዐት ላይ እንደሚገኝ ለሚጠይቅ መልሳችን "ለአዲስ ሥርዓት ጅማሮ ፦የተባበረ ትግልና የሕዝብ አመጽ ጉዳይ፤" ይሆናል ።ይህም የትግሉን መለስተኛ ግብ ከማመላከት ወዲያ ለስኬቱም የተጓደሉትን፤ ወሳኝ ግና ተሰናሳይ ፤ግብዐቶች አጥርቶ እንደሚያሳይ እምነታችን ነዉ።

የዘረኞቹ የአገዛዝ ዘመን ለፍጻሜዉ መቃረቡን ለማጠየቅ ብዙ መልፋት አያሻንም ። በየዕለቱ ግዘፍ ከሚነሳዉ የሕዝብ ቁጣና ምሬት አንጻር ፤ የሥልጣናቸዉ መሠረትና ግድግዳ እየተሰነጠቀና እየተናደ መሆኑን የተረዱቱ ወያኔዎችና ለከርስ አደር ሎሌዎቻቸዉ እርስ በርስ በመባላት ላይ መሆናቸዉን መጥቀሱ ይበቃል ። የዘመን ስላቅ ሆኖ፤ በፋሺስት ጣልያን አገዛዝ ፍጻሜ ላይ በተተነበየዉ ምሳሌ፤ ሕዝባችን ገና ከወዲሁ ፤ "አርኩም ይሄድና ....ገንዘቡም ያልቅና" እያለ መተረት ከጀመረ ሰነባብቷል ። እነሆ ሥርዓቱ መሬት እየከዳዉ መሆኑ የገባቸዉ በርካታ የአገር ጠንቆችና "አይተነዉ ጊዜ" ባይ ባንዳዎች ሰልፍ ለዉጠዉ ከሕዝቡ ጋር መሰለፋቸዉን እየለፈፉ ነዉ ። ይህን በመሰለዉ ወሳኝ የታሪክ ቅጽበት ለተተኪዉ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ምጽአት በቆሙት ወገኖች የሚደረገዉ ትግል ይበልጥ የከረረና ኃይሉን አጠላልፎ የተባበረ ወያኔን የሚበላዉ እሣትም ፍም ነበልባሉ ከሩቅ የሚጋረፍ መሆን እንደሚገባዉ ግልጽ ነዉ ። ይህ እዉነታ ግና መሬት ላይ ካለዉ ሁኔታ ጋር ፈጽሞዉኑ የሚገጥም አይደለም ። እስኪያሰለች የተደጋገመዉን አባባል መድገም ባይሆን ፤ የዘረኛዉና አምባገነናዊዉ ሥርዓት ህልዉና ከዉድቀት አፋፍ ተንጠላጥሎ የመዝለቁ ዋና ምስጢር ከራሱ ጥንካሬ ሳይሆን ከተቃዋሚዎቹ ደካማነት ጋር በቀጥታ የተያያዘ ነዉ ።

የከዚያ ቀደሙ ሁሉ ቀርቶ ፤ ከወያኔ ጋር ከተደረገዉ የሃያ ሁለት ዓመታት ትግል እንኳ አንዳችም ትምህርት ያልቀሰምን እስኪመስል ድረስ፤ ዛሬም ሰልፋችን መስመር ያልለየ -የትርምስ ነዉ ። ሌቱን ስንገነባ ያደርነዉን ቀን ላይ ስናፈርስ የምንዉል እንመስላለን ። አመለካከታችን ረገረግ ፤ የምንወጥነዉ ረጋ ሠራሽ ነዉ ። በእሣት የተፈተኑትን የራሳችንን ጀግኖች ምሳሌ አድርገን በመከተል ፈንታ፤ የወያኔን ሰርጎ ገቦች በዉዳሴ እያንቆሻበልን እናብዳለን ። እጅ ላልገባ ግዳይ "ጉሮ ወሸባዬ" እያቀነቀንን እስክስ ማለት ይቀናናል ።ከሕዝባችን ጋር ቆመን በሀገር ጠላት ላይ ጦር ከመስበቅ ይልቅ ጉልበተኛ ባዕዳንን ጠብ ለማይል ርዳታ መማጸን ይቀናናል ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለወያኔዎችና ለአገዛዛቸዉ ያለዉን ምሬትና የበቃኝ ባይነቱን ያህል፤ የሚሻዉን ለዉጥ በአፋጣኝ ያለማየቱ ዋና መንስዔም ከነዚሁ ድክመቶቻችን ጋር በቀጥታ የተቆራኘ መሆኑ ሊታበል አይችልም ።

ሕዝባዊዉ ትግል ደጋግሞ ቢቀለበስ ፤" አዲስ ቀን ያወጡልን" ብለን የተማመንባቸዉ "ዶሮ ሳይኳኩል" ደጋግመዉ ቢከዱን ፤ ከነዚሁ ደካማ ባህሪያት መሃከል ነዉ ለተደጋጋሚዎቹ ሽንፈቶቻችን ማሳበቢያዉን መፈለግ ያለብን ። ከኢትዮጵያ ጠላቶች ጋር "ነጠላ ሲጋፈፉ" የተገኙና ጥፋተኛነታቸዉ ተኮንኖ ሲጠየቁ ፤ ሁኔታዉን በማስተባበል ወይም ይቅርታ በመጠየቅ ፈንታ ... "ቢሆንሳ ?/.....ምን ይጠበስ ?" ብለዉ በትዕቢት የሚመልሱ ጋጠወጦችን በተቋም ደረጃ ያደራጃቸዉም ፤ወዳጅ ባላንጣን በቅጡ ሳይለይ በየዋህነት የተበተነዉ፤ የኛዉ ገንዘብ ነዉ ። ዛሬ ዛሬ በልጆቿ እኩልነትነትና የወል ሱታፌ መሠረት ላይ አንድነቷ የጸና ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ዕዉን ለማድረግ ያለንን ራዕይ ሳይቀር በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ሲሳለቁበትና ሲዘባበቱበት የሚደመጡትን አፈ -ጮሌዎችና የወያኔ ቅፍቅፍ ጎሠኞች ፤ያልፈጠረባቸዉን "ታጋይነት" ሽልመን በይበልታ ያጀገንን-ያገዘፍናቸዉ እኛዉ ራሳችን መሆናችን ያሳዝናል ፤ያስቆጫልም ። እንደዘበት "ቁጭ ብለን" የሰቀልናቸዉን እነዚህን የዘመን ጉዶች መልሶ ለማዉረድ መንጠራራቱ በትግሉ ላይ ተደራቢ ሥራ መሆኑ ብቻ ሳይሆን " ሁካታና ጫጫታዉ" ጥቂት የማይባሉ የዋሃን የሚነሆልሉበት ሁነት መሆኑን ከታዘብን ዉለን አድረናል ። ተመሳስለዉ በመስረግ፤ በትግሉ ማሳ ላይ እንክርዳድ መዝራትን ሥራ አድርገዉ የያዙ የወያኔ የደህንነትና የስለላ መረብ ቅጥረኞች መሀከላችን የሚንቀሳቀሱ መሆኑ ለአፍታ እንኳ ቸል ሊባል የማይገባዉ እዉነት ነዉ ። ጎሰኛዉ አምባገነናዊ አገዛዝ በሕዝብ ዐመጽ እየተደፈረ ሲሄድና እንደሥርዓትም የመሞቻዉ ዕለት ይበልጥ እየቀረበ ሲመጣ ደግሞ የሥርጎ ገብነቱና ዉዥንብር የመንዛቱ ወያኔያዊ ተግባር በገንዘብና በሰዉ ኃይል ይበልጥ ጎልብቶ እንደሚካሄድ አያጠራጥርም።በዚህ ረገድ በ፩፱፻፺፯ ዓ.ም ከተጨናገፈዉ የሕዝብ መነሳሳት ብዙ ብዙ ልንማር በተገባን ነበር ። አልሆነም ፤ ዛሬም ከዚያን መሰሉ አዙሪት አልወጣንም ።

እነሳሳችን ለሀገርና ለወገን የሚበጅ ታላቅ ዓላማ አንግበን ስለመሆኑ እርግጠኛ እስከሆንን ድረስ፤ ቢያንስ በተራ የአዕምሮ ንቃት ሊመከቱ ከሚችሉ የጠላት አፍራሽ ዘመቻዎች ሕዝባዊዉን ትግል መታደግ ይኖርብናል ። ለብዥታና ለድንጋሬ ቦታም ሆነ ጊዜ ልንሰጣቸዉ አይቻለንም ። የተፋጠጥነዉ ፍጹም ጸረ-ኢትዮጵያ ከሆነና ሕዝቡን በድንነትና በጎጥ አጥር ከልሎ እያናከሰ እስከተቻለዉ ዘመን አገዛዙን ሊያዘልቅ ከቋመጠ ቡድን ጋር ነዉ ። አቸናፊነቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ መሆኑ እርግጥ ነዉ ። የድሉን ቀን ለማራቅ ግን ልዩ የይለፍ ፈቃድ የተሰጠዉ ግለሰብም ሆነ ቡድን እንደሌለ በዉል ሊታወቅ ይገባል ።

ሕዝባዊዉ ዴሞክራሲያዊ ትግል ያቸንፋል!
ኢትዮጵያ፤ በነጻነቷ ኮርታ ለዘለዓለም ትኑር!

# ዜና ከተባለ

መስተዋት ከድሬ

### ዜና ከተባለ ይነገር ይሰማ
### ወንዙ በሞላበት ሰው ውሀ ሲጠማ

ወሩ የትግል ሆኖ ተስፋን ፈንጥቆብናል ። ለጨቋኝ አገዛዝ የሁሌም አማራጭ አፈና ነውናም ብዙ ዜጎች መስዋዕትነትን ተቀብለዋል ። የፈተናውና የመለያው ፤ማን ታጋይ፤ ማን ሀገር ወዳድ፤ ማን አስመሳይ መሆኑ ሊታወቅ ነው ማለቱ ይቻላል ። ወያኔ በዘርፈ ብዙ የቅውጢ ቀን እንቅስቃሴ ላይ አለ። በአንድ በኩል ሆድ አደሮችን በቤት/ኮንዶሚኒየም ሊደልል ተምዝገቡ እያለ ሀፍረት ቢሶቹም በየወያኔው ኤምባሲ ሲስጡ ታይተዋል ። በሌላ በኩል የተቀነባበረ ዘመቻ በሚታገሉ ሙስሊሞችና ድርጅቶች ላይ ከፍቷል ። ተላላውም ቅጥረኛውም የሙስሊም ኢትዮጵያውያንን ሰላማዊ ትግል በጽንፈኝት ለመፈረጅና የክርስቲያን ዜጎችን በተለይ ለማስፈራራትና ከወያኔ ጎን ለመለጠፍ እየተራወጡ ናቸው ። ከዚሁ ተያይዞ ደግሞ በተወሰኑ ድርጅቶች ላይ በጣም የተጧጧፈ የስም ማጥፋትና የመከፋፍል ዘመቻ እየተካሄደ ነው ። በኢሕአፓ ላይ በወያኔ አራጋቢነት የተከፈተውንና እነ መረራ ጉዲናና የቀድሞ የመኢሶን መሪዎችም የተሳተፉበት ያለውን ዘመቻ ያጠኗል ። የስብሐት ተላላኪ ሆኖ የቆየው ወጣት ጋዘጠኛ በሉኝ ዳግማዊ ልደቱ ግለሰብ ከወደ አዲስ አበባ ነጋ ጠባ የሚከትበውንም ማጠን ተገቢ ነው ። ከዚህ ዘመቻ በተያያዘ ደግሞ ወያኔ ያው የለመደውንና ለስልጣን ያበቃና ያቆየውን አፈናና እመቃ እያስፋፋ ነው።

ማንነቱና ይዘቱ አጠያያቂ ነው የሚባለውን ሰማያዊ ፓርቲ (በቅርቡ ከሕጋዊ ተቃዋሚዎች ስብስብ አባረውታል) ለእሁድ ሰልፍ ሲጠራ በውዳመ ቢሮው ተሰብሮ ከሙቶ ያልነሱ መሪዎችና አባላትም ተያዙበት ተብሏል ። ከዚያ በላይ ሙስሊሞችም በዚሁ ጊዜ መታሰራቸውም ተዘግቧል ። የሙስሊሞች ሰላማዊ እንቅስቃሴ በጽናት በመቀጠሉና ለአፈና አልመንበርከኩ ምሳለና አርአያ እንዲሆን አድርጎታል ። በባዕድ ሀገሮችም ቢሆን እንዲሁ ። በዚህ ላይ መገንባትና የካቲታዊ ሰፊ ይዘት መስጠት አስፈላጊ መሆኑ ደግሞ አከራካሪ አይደለም ። ይህን በተመለከተ ታጋይ ድርጅቶች ከሚታገለው ሕዝብ ጎን ሲቆሙ ያ ቀይ ሽብር ኦሮሞን ለመጨረስ ደርግና ኢሕአፓ የፈጠሩት የሀበሻ ተንኮል ነው ሲል የነበረውና የቆየው ኦነግ ደግሞ " የእኔ ሕዝብ" ተጠቃ በሚል የሙስሊሙን ትግል እብደተ ጃዋርን ሊለግሰው ሲሞክር ታይቷል። አሁንም ክፍፍል ሰፍኖ አለ ። አሁንም ክፍት የፖለቲካ ዕድልን ለመጠቀም አእመቻል አለ ። ይህ ሁሉ ይታረማል ብሎ ኢትዮጵያዊው ተስፋ እያደረገ ባለበት ሁኔታ ሕዝብንና ድርጅቶችን ለመከፋፋልና ለማዳከም የተከፈተው ወያነያዊ ዘመቻ በቀላሉ መታየት የሌለበት ነው ።

ኤኮኖሚው በ ሰባት በሙቶ ዕያደገ ነው በተባለበት ሀገር የድህነት ደረጃው ደግሞ ወደ ሰማያ ሰማያት መጥቋል ቢባል ስህተት አይደለም ። በፖለቲካ አፈና ስርዓት ኤኮኖሚን ማሳደግ ይቻላል (ይህን ባዮች ደቡብ ኮሪያን፤ ቻይናን፤ ሲንጋፖርን መጥቀስ ይወዳሉ) የሚሉትን ወያኔ ቢያስተጋባም ይህ የ ኤኮኖሚ ዕድገት የሚባለው ምትሃት ሆኖ አለ። ይህን በሚምለከት የሰፊው ሰርቶ አደር ህዝብ የወደቀ የኑሮ ይዞታ (ጉርሻ በብር ከሀምሳ ከነ ስብሐትና አዜብ ሚሊዮኖች እየተነጻጸረ) አለ ለሚባለው የ ኤኮኖሚ ዕድገት መለኪያ ሆኖ መቅረብ ያለበት ነው ። አልቀየር ብሎ ያለውና ሁሉም የሚስማማበት ግን ያው አገዛዙ ከአንድ ብሄረሰብ ከተውጣጡ አርመነ ገዢዎች መያዙና ስርዓቱም የጭፍን ብዝበዛ መሆኑ ነው ። በገዢዎች መሀል በተከሰተው የስልጣን ሹኩቻ የሙስናዋ ዕቴጌ ቅርብ ወዳጅ የተባለው የጸጥታ ሀላፊ ወልደስላሴ ዘብጥያ ሲወርድ አዜብም ይዛው ከነበረችው ቁልፍ የወያኔን ኩባንያዎች የመቆጣጠሪያና የመዝረፊያ ቦታዋም እንድትለቅ ተገዳ የ ኤፈርት ተቋም ሀላፊ የቿንሌባውና ዘረኛው አዛውንት ጓደኛ እንዲሆን ተደርጓል ። በመለስ ፋውንዴሽን ወይ ተቋም ስም የሕዝብን ገንዘብ ለመዝረፍ ካርቱም ድረስም የሄደችው አዜብ የታሰሩ ጓደኞችዋን ወደ ቃሊቲ ልትቀላቀል ነው የሚለው ግምት ግን ቁርጥ ያለ መልስ የሚሰጠው አይደለም ገና ። በተያያዘ ዜና ግን በአባይ ወልዱ የትግራይ አስተዳዳሪና በብርሃነ ኪዳነ ማርያም (ማረት--የትግራይ መረዳጃ ማህበር-- ሀላፊ) የሚመራ የሰባት ሰው ልኡክ (ዳንኤልና ተክለወይኒ አሰፋም አሉበት) ወደ አሜሪካ ዘልቆ የትግራይ ተወላጆችን ብቻ በየከተማው በመሰብሰብ ገንዘብ አዋጡ፤ በላያችን ላይ አደጋ መጥቷልና ተባበሩን ወዘተ በሚል ያቀረቡት ጥሪ ብዙ ሰሚ አለማግኘቱ ተዘግቧል ። በሕዝብ ገንዘብ ይሰራል የተባለውም የአባይ ግድብ በገንዘብ ዕጥረት ዳዴ እያለ ነው ሲባል በሌላ በኩል ግብጽ በፖለቲካ ውጥረት ውስጥ በመግባቷ ገንጣዮችን በመርዳት መበጥበጥ ብላ ያቀደቸውና በዛቻ መልክም ያቀረበችው ከሙርሲ ጋር ለጊዜውም ቢሆን ውድቀት ደርሶበታል ማለት ይቻላል ።ይህ በዚህ እንዳለ ደግሞ የወያኔም የሱማሌ ወረርና ጀብደኝነት እየተነፈስና ግቡን አልመታ እያለ ነው ተብሏል ። ተሸነፈ የተባለው አል ሸባብ አሁንም ህልውናውን ጠብቆ በሽብሩ የቀጠለ ሲሆን በወያኔና በምዕራቦቹ ድጋፍ የተመሰረተው የሞቃዲሾ መንግስትም ደካማ ከመሆን አላለፈም ። የሱዳኑ በሺር በአፋር አማጽያን (ፍሩድ) ጥቃት እየደረሰበት ካለው የጅቡቲው ገሌህ በተሻለ ሁኔታ ላይ አይደለም ። የደቡብ ሱዳኑ ሳልቫ ኪርም ሚኒስቴሮቹን ሁሉ ኣባሮ የዚችን አዲስ ሀገር የመረጋጋት ዕድል አፈር አብልቶታል ። ከወደ አስመራ ደግሞ ምንም ደግና ተስፋ ሰጪ ወሬ ብቅ አላለም ከነዋሪዎቹ አንጻር ። በዚያ ያሉ የወያኔ ተቃዋሚዎች ግን ወያኔን በትጥቅ ልንፋለመው እየቀረብን ነው ማለታቸው ሳይጠቀስ አያልፍም።

* ከኬንያ ተይዞ የፖለቲካ አስረኛ ሆኖ የቆየው ተስፋሁን ጨመዳ በደረሰበት አስቃቂ ስየል ሕይወቱ ማለፉ ታውቋል። አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተቋሞች የወያኔን እስር ቤቶች ለመጎብኘት ወይም ይዞታቸውን ለማጋለጥ በቂ ትኩረት አለመስጠታቸው የሚታወቅ ነው። ይህን በተመለከተ በ አውሮፓ የስራ ጉብኝት እያደረጉ የቆዩት የ ኢፖእአኮ ፕሬዚዳንት አቶ አሊ ሁሴን ሰፊ እንቃስቃሴ አድርገዋል ። በወያኔ እስር ቤቶች ስየል የተለመደና አስቃቂ ነው ።

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ምን ይሰማ ......አገር?



"የኢሕአፓን መጨረሻ ማወቅ የዚህ ሬድዮ ኢንተረስት (ፍላጎት) ነዉ ፤......(ይህንን በተመለከተ ) ከሬድዮ ዉጪ አናግሩኝ ። ብትፈልጉም ስብሰባ ጥሩኝ ፤ ኮንፈረንስም አስቀምጡኝ ።"
(የአበበ በለዉ ሬድዮ በኦገስት ፲፯ ቀን ፪፻፲፫ እወጃዉ ካስተላለፈዉ የተቀነጨበ ።)

* ፍላጎትህንማ ባትናገረዉም ይጠፋናል ብለህ ነዉ?? የገላጋይነት ሚናህም በቤተክህነት ብጥብጦች ልምዱን ያካበተ ዝነኛ መሆኑን ድፍን ዋሽንግቶን ያዉቀዋል ። ከኢሕአፓ ጋር ተቀምጦ ለማሸማገል ግብዣ መጠበቅህ ግን ራስን ከአቅም በላይ የማተለቅ አባዜ ከተጠናወተዉ አዕምሮ የመነጨ መስሎብሃል ።...ግን ከምርህ ነዉ??

//

"ኃይሌ የጃንሆይን መኝታ ክፍል ከተመለከተ በኋላ አሰበ ።ከአፍታ በኋላ አልጋቸዉ ላይ ተቀመጠ ። አልጋዉን ወደላይ ወደታች ካወዛወዘ በኋላ "ይህንን ቤተ መንግሥት" በማለት እንደሚኖርበት ዛተ ።"
(ጎልጉል የድረ ገጽ ጋዜጣ ጁላይ ፳፬ ቀን ኃይሌ ገ/ሥላሴን በሚመለከት ምንጭ ጠቅሶ የዘገበዉ )

*አልጋዉ ላይ ከእርሱ ያናነሱቱ ተደላድለዉ በማዬቱ ተገፋፍቶ ያለዉ ሊሆን ይችላል ።.... ግን ግን ሯጩ ሰዉ ፋታ አግኝቶ፤ " አልጠግብ ባይ ሲተፋ ያድራል፤" ብለዉ የተረቡትን ወገኖች ሰምቶ ይሆን ?!

//

"የዱር እንስሳት ጥበቃ ፖሊሲን የሚያስፈጽሙ ህጎች ክፍተት አለባቸዉ ተባለ ።"
(ሪፖርተር ጁላይ ፳፩ ቀን ፪፻፲፫ የዘገበዉ ዜና ፤)

* "ወያኔ እኳኳላለሁ ብላ ዐይኖቿን አጠፋች ፤" ያለዉ የሻቢያዉ ኢሳያስ ነበር?...እዉነት ብሏል ። ወያኔን ከፈጣሪዋ በላይ የሚያዉቃት አይገኝም።

//

"......ሌላዉ ስለነጻነት ጉዳይ ነዉ የሚነገረዉ ። ድንቄም ነጻነት። ቅድም ተነስታችሁ ስለሰማዕታት የህሊና ጸሎት ስታደርጉ አይቻችኋለሁ ። እኔ ግን አባቱ ለምን እንደሞተ አልገባኝም ። ወንድምና እህቶቼም ለምን እንደሞቱ አይገባኝም ። በፍጹም ጸልዬ ተነስቼ አላዉቅም ። እኔ ይህ ቋንቋ አይገባኝም ። ነጻነት ሳገኝ ፤ ያኔ ሲገባኝ ለጸሎት እነሳለሁ ።"
(አንድ ከትግራይ ወረዳ የመጣ ወጣት በመቀሌዉ የመድረክ ስብሰባ ላይ ተገኝቶ ያቀረበዉ አስተያየት ፤ የአሜሪካ ድምጽ ሬድዮ ኀምሌ ፲፫ ቀን ፪፻፫ ዓ.ም እንደዘገበዉ ፤)

- "የተከዜን ዉሀ የጠጣ ሁሉ ወያኔ ነዉ ፤" ማለት የሚቃጣችሁ ወገኖች ፤የዚህን ወጣት ምሬትና ጩኸት፤ ቢዘልቃችሁ አድምጡለት ።

ከገጽ 3 የዞረ

በውጭ ሀገር ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን በሰብአዊ መብት ጉዳይ ሰፊ ወያኔን የሚያጋልጥ እንቅስቃሴ ማድረግ ይጠበቅባቸዋልም ተብሏል ።

*በውጭ ሀገር ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን በሰብአዊ መብት ጉዳይ ሰፊ ወያኔን የሚያጋልጥ እንቅስቃሴ ማድረግ ይጠበቅባቸዋልም ተብሏል ።

*የወያኔ አባሎችና ካድሬዎች በባለስልጣኖቹ ግንባር ቀደምነት የሀገሪቷን ታንታሊየምና ኦፓል ምርት ወደ አውሮፓ እያጓጓዙ በሸጥ ላይ ናቸው ሲሉ ውስጠ አዋቂዎች አጋልጠዋል ። የጫቱን የወጭ ንግድ እነ አዘብ፣ ባጫ ደብልና ለሎችም እንደያዙት ሁሉ በህንድና በቻይና ሲጎረፍ የከረመውን የኦፓል ንግድ ግለሰብ ነጋዴዎች እንዳይሳተፉበትም ገደብ እየተደረገ ነው የሚል ጥቆማ አለ ።

*ዶክተር መረራ ጉዲና የሕይወት ታሪኬ በሚል መልክ ያሳተሙት መጽሀፍ በሀያሲዎች በልዩ ልዩ ፈርጅ (ብዙ የሆሄያት ስህተት፣ የተዛባ መረጃ፡ አከራካሪ "ሀቆችን" በመያዙ) በአሉታዊ ተተችቷል ። ዶክተር መረራ በደርግ ዘመን የመኢሶን አባል የነበሩ ሲሆን (ታስረውም ነበር) የድርጅታቸውን ስም እንኳን በትክክል አልጻፉትም ተብለው ተወቅሰዋል ።በፖልቲካው መድረክ የተሳተፉና አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ሚና የነበራቸው የየበኩላቸውን መጻፋቸው በዚህም በዚያም አስተዋጾ ሊኖረው ቢችልም በሀሰት ላይ የተመሰረተ "ታሪክ" መጻፍና የታገሉትን ታሪክ ማበላሸት በዝምታ መታለፍ የሌለበት ነው ።

* የፊንላንድ አምባሰደር ሆነው በኢትዮጵያ ለአራት ዓመት የቆዩት ሚስተር ሊዮ አላስቪርታ የወያኔ አገዛዝ ጸረ ደሞክራሲና የስብአዊ መብት ረጋጭ ነው ሲሉ መኮነናቸው በፊንላንድ የውጭ ጉዳይ መጽሔት ውስጥ ተዘገበ።

* የሙስሊም ኢትዮጵያውያንን ትግል ለማፈን ወይም ለማደናቀፍ የሚጥረው ያው የተጠበቀው ወያኔ ብቻ ሳይሆን የግንጠላና ጭፍን ጥላቻ አጀንዳ ይዘው የሚንቀሳሱ ክፍሎች መሆናቸውን በሲአዬው ስታንፎርድ ዩኒቨርስቲ ሰልጥኖ በማደናገር ስራ የተሰማራውና አዋቂ በሚልም የተሻሸጠው ጃዋር መሀመድ ምሳሌ ሆኖ ውግዘትን ተከናንቧል ። እሱ ብቻ ሳይሆን በልዩ ልዩ አኑን አንጃ የተሰለፉትም ቢሆኑ በጋራ ሰልፎችና ስብሰባዎች ላይ የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ ሳይሆን የኦነግ አርማ ይውለበለብ በሚል ትግሉንና የኢትዮጵያ አንድነትን ካቆራኙ ክፎሎች ጋር ልዩነት በመፍጠር የጋራ ትግሉን እየከፋፈሉት ናቸው ። ይህን ጎጂ አቅዋም ሁሉም ሊታገለውና ጃዋሮችንም ወደ ፖለቲካ ምድረበዳ መወርወር ሲገባው በተለይም ሙስሊም ኢትዮጵያውያን ትግላቸው በገንጣዮች፣ የጥላቻ አራማጆችና የወይኔ ቅጥረኛ ከፋፋዮች እንዳይነጠቅ ከክርስቲያን ወገኖቻቸው ጋር ሆነው መታገል ግዴታቸው ነው ።

ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ!
አፍራሾችን አሸንፈን በጋራ ትግል ወያኔን እንጣል !!
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!!

**የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)**
**Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)**

ነሐሴ 14 ቀን 2005 ዓ.ም.

**ለክርስቲያን ወገኖቻችን ማሳሰቢያ**

ሀይማኖት የግል ነው ሀገር የጋራ ነው፤ ፖለቲካና ሀይማኖት አይደባለቁ በሚሉት መሰረታዊ መርሆዎች የሚያምነው ኢሕአፓ በወያኔ የተቀነባበረውን ከፋፍለህ ግዛና ጸረ ሙስሊም ኢትዮጵያውያን ዕቅድ ክርስቲያን ኢትዮጵያውያን ነቅተውና በጋራ ሆነው እንዲያከሽፉ በ እጅጉ ያሳስባል፤ ጥሪም ያደርጋል ።

ወያኔ የሙስሊም ወገኖቻችንን መብት ነፍጎ፤ በላያቸው ላይም ባዕድ እምነት ሊጭንና በሀይማኖት ጉዳያቸው ላይ ጣልቃ ሲገባ የጀመሩት የሚደገፍ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ለማክሸፍ ያልሞከረው ሴራና ያልከፈተው ዘመቻ የለም። በተለይም ክርስቲያኑን ኢትዮጵያዊ ለማስፈራራትና ከወገኖቹ ሙስሊሞች ጋርና ጎን እንዳይሰለፍ ለማድረግ የሀሰት ቪዲዮውችንም እየቀረጸ፤ እንቅስቃሴውን ሽብርተኖች ከሚላቸው ሊያቆራኝ እየሞከረ፤ አፈና እያካሄደ በመጠነ ሰፊ ፕሮፓጋንዳዎች በማጀብ ወዘተ ሰፊ ዘመቻን ከፍቷል። ዋልድባን ለባዕዳን የሸጠው ወያኔ ክርስቲያኑን የደለለ እየመሰለው ድሮ በታሪክ ተቃጠሉ የሚላቸውን ቤተክርስቲያኖች መስራት የሚልም እደናጋሪ ቅስቀሳ መጀምሩንም እናያለን። ዋልድባ ሲደፈር ለሰልፍ ብቅ ብለው የማያውቁና በወያኔ ቁጥጥር ስር የገቡ በባዕድ አገር ያሉ ቤተ ክርስቲያኖች ሀላፊዎችም የዚሁ ጸያፍ ዘመቻ ተባባሪ ሆነው ጸረ ሙስሊም ቅስቀሳውን መጀመራቸውንም ታዝበናል። ይህንን በዝምታ የምናልፈው አይደለም። ጽንፈኝነትን መቃውም--ከየትም ይምጣ ከየት--የሚገባ ቢሆንም መብታችን ይከበር የሚል እንቅስቃሴን ግን በወያኔ ቀስቃሽነት በጽንፈኛነት ፈርጆ ለወያኔ ተንኮል ሰለባ መሆን የሚገባ አይደለም። ወያኔ የሀሰት ወረቀቶችንና ክሶችን አሰራጭቶ አልሰራ ሲለው ከዚህ ቀደም እንዳደረገው ሁሉ ቤተክርስቲያኖችን አቃጥሎና ምዕመናንም ገድሎ በሙስሊሞች ላይ ለማላከክ የሚጥር መሆኑን መጠበቅ ያስፈልጋል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን በሀገርም በውጭ ሀገርም በጎጥ ሳይቀር ክፋፍሎ የሚያፈራርሰውና በቅጥረኞቹ ቁጥጥር ስር የሚያስገባው የአማኞች ዋና ጠላት ወያኔ እንጂ መብታችን ይከበር ያሉና መስዋዕትነትንም እየከፈሉ ያሉ ሙስሊም ወገኖቻችን አይደሉም። በፍትሐዊው እንቅስቃሴ ውስጥ ሰርገው ገብተው ጥላቻና እልቂትን የሚጋብዙ አስመሳዮችና ጽንፈኞች ደግሞ ተልዕኮአቸው ወያኔያዊ ነውና እነዚህንም ማጋለጥና ከሕዝብ ትግል ማራቅ አስፈላጊና ወቅታዊም ነው።

ሕዝብ ከህዝብ የሚያጣላውን የወያኔ ዘመቻ ሕዝብ ክርስቲያን ከቶምና መቼም ቢሆን መደገፍ የለበትም። የወያኔን ተንኮልና ሴራ በሀይማኖት ሽፋን ሊይራግቡና ሕዝብን በሀይማኖት ሊክፋፍሉ የተነሱትንም --በውጭ ሀገር ሆነ በሀገር ቤት-- አጥብቀን በጋራ እንድንታገላቸው ኢሕአፓ ጥሪውን ያስተላልፋል። ምዕመናን መብታችውንም ቤተ ክርስቲያኖችንም መስጊዳቸውንም ማስከበር አለባቸው። ክርስቲያኖች ጸረ ሕዝብ ጸረ ኢትዮጵያ ከሆነው ከወያኔ ጎን ሳይሆን ከሙስሊም ወገኖቻቸው ጎን በመቆምና የተጀመረውንም ትግል በማጀብ ለመላ ኢትዮጵያዊ ዜጋ መብት እንዲታገሉም እነሆ ዳግም ጥሪው ቀርቧል።

ጸረ ሕዝብ ሀይል የሆነው ወያኔ ነው!
ለወያኔ ከፋፋይ ተንኮል ሰለባ አንሁን!!
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል !!!

**የቦረና ነጌሌዎቹ የኢሕአፓ ወጣቶች ሕዝባዊ ገድል በጨረፍታ ቅኝት**
**(ምንጭ መጽሀፍ ፤ "ያልታደለዉ ትዉልድ- እዉነተኛ ታሪክ፤)**
**(ደራሲ ፤አብዲ አብዱላሂ)**

## ስደት -ወደ ባዕድ አገር፤

(ካለፈው የቀጠለ)

"ገዛ ባድማዉ የተኛዉን በሬ
ነካክተዉ ነካክተዉ አደረጉት አዉሬ ፤"

ይላል ፤ በትዉልድ አገር የመገፋትን ምሬት አጉልቶ የሚያሳየዉ ሕዝባዊ ግጥም ። እናም ተከፋሁ ። በገዛ ሀገሬ ሰብዐዊ መብቴንና ነጻነቴን ከተገፈፍኩ ምን አገር አለኝ ብዬ እቀመጣለሁ?/...ዕምባ ሳይሆን ደም እያለቀስኩ ፤ የሚደርስብኝን ችግርና እንግልት ተቋቁሜ ሀገሬን ለቅቄ ለመሰደድ ወሰንኩ...ወደ ሶማሊያ ።

የጉዞ ባልደረቦቼ እግረ ጀቢራ ባላገሮች ናቸዉ ። መንገዱ በዋዛ ይጠቀለልላቸዋል ። ከተሜዉ ቅንጡ እንደምንም ተበራትቼ የመጀመሪያዉን ሳምንት ጉዞ ተወጣሁት ። መንገዱ ማለቂያ አልነበረዉም። የሁለተኛው ሳምንት የቀንና የሌት ጉዞ እጅጉን አድካሚ ነበር ። ብቻዬን በረሃ ዉስጥ እንዳልቀር የሞት ሞቴን ተንከላወስኩ ። የሠራ አካላቴ ዉልቅልቁ ወጣ። በሌሊቱ ጉዟችን ላይ የግራዉን እግሬን እንጨት ክፉኛ ወጋኝ ።እንጨቱ ተሰብሮ ሥጋዬ ዉስጥ በመቅረቱ ዕብጠቱና ሕመሙ አላላዉስ አለኝ ። ባላገሮቹ ባልደረቦቼ ለፈዉስ የመረጡልኝ የህክምና ዘዴ በጣሙን አስደነገጠኝ ። ግን አልቀረልኝም። ሌላ ምርጫም አልነበረኝም ። አንደኛዉ ተጓዥ መታጠቂያዉ ላይ ያገነደረዉን ጩቤ መዝዞ ቁስሌን ለሁለት ሰነጠቀልኝ ።እሪ ብዬ ጮህኩ ። ጩኸቴን ታግሰዉ እንጨቱን አወጡልኝ ። ቀጥለዉም በሚደማዉ እግሬ ላይ የባትሪ ድንጋይ ከስክሰዉ ዱቄቱን ከነሰነሱበት በኋላ በቅጠልና በአሮጌ ጨርቅ ጠቀለሉልኝ ። ያ ቀድዶ ጥገናቸዉ ጉዞዬን ለመቀጠል አስቻለኝ ።

የኢትዮጵያን ድንበር ለማለፍ የሶስት ቀናት መንገድ ሲቀረን እግሬ ተሞሸላለቀ ። በምሬት አነባሁ። የባላገሮቹ ህክምና አስፈላጊዬ ሆኖ በመገኘቱ በተለመደዉ መንገድ ፤እየጠዘጠዘ አላራምድ ያለኝን የእግሬን ዕብጠት አፈነዱልኝ ። አያይዘዉም በተለይ በጉዟችን መደምደሚያ ላይ በከፍተኛ ፍጥነት መደረግ ያለበትን የመጨረሻውን ሌሊት ድንበር አቋራጭ ጉዞ መወጣት ካልቻልኩ እነርሱንም ጭምር ለጠላት አሳልፌ የምሰጣቸዉ መሆኑን ቁጣ ቅልቅል አስጠነቀቁኝ ።

ሞት ካልቀረ ፤ "የዴሞክራሲ መብቶች ያለገደብ ይከበሩ/" የሚለዉን መፈክር እንዳነገብኩ በጓዶቹ መሃል ወድቄ ቢሆን ኖሮ ምንኛ የክብር ሞት ይሆንልኝ እንደነበር አሰብኩ ። የጓዶቼን መሥዋዕት ማሰቤ አበረታኝ መሰል ፤ ከየት መጣ የማልለዉ ኃይል በቅጽበት አገኘሁ ።የሀገሬን ድንበር ተሻግሬም ሶማልያ ገባሁ ።

# ትላንትና

በሶማልያዋ የቡልሀዋ ከተማ ዉስጥ ለሶስት ሳምንት ያህል ቆዬሁ ።ጉዞዉ ምን ያህል እንዳደከመኝ የታወቀኝ ያኔ ነበር ። ቀን ቀን በተቀመጥኩበት ወይም በተጋደምኩበት መንፈሴ ይቃብዛል ። ጥሻ ለጥሻ ፤ ቆንጥር ለቆንጥር በሃሳብ ያዋትተኛል ።ሌሊቱን ደግሞ አስፈሪዉ ቅዠት ይተካና ከሸሸሁት የደርግ ጉያ መልሶ ይከትተኛል ። እግሮቼ አርቀዉ ቢወስዱኝም ነፍሴ ከጭንቅና ከሰቀቀን አልዳነችም ። ብቻ እንደምንም ከጊዜ ጋር አገገምኩ ። ተከታዩ የጉዞዬ ግብ ታላቅ ወንድሜ መሀመድ ወደሚገኝበት ሥፍራ መሄድ ነበር ። ኢትዮጵያ ዉስጥ መምህር የነበረ ሲሆን ከኔ ቀድሞ በስደት ወጥቶ ሞቃዲሾ ዉስጥ ይኖር ስለነበር ወደዚያዉ አቀናሁ ።

ከሁለት ዓመታት ቆይታ በኋላ ፤ በሀገሬ አቋርጬዉ የነበረዉን ትምህርቴን ሞቃዲሾ ዉስጥ ጀመርኩት ።ትምህርቴን እንዳጠናቀቅኩም በጌዶ ክ/ሀገር በምትገኘዉ ገርበሀሬ ከተማ በመምህርነት ተመድቤ ለሦስት ዓመታት አገለገልኩ ። የደርግን የጭካኔ በትር አምልጬ ኑሮዬን ብጀምርም በወቅቱ በሶማሊያና በኢትዮጵያ መሃከል በነበረዉ ጦርነት ሳቢያ የነበርኩበት ከተማ በኢትዮጵያ ተዋጊ ጄቶች ለሦስት ተከታታይ ጊዜ በመደብደቡ ዞር ያልኩ እንጂ የሸሸሁ አልመስልህ ብሎኝ ተቸግሬያለሁ ።በተለይ በመጨረሻዉ ድብደባ ፤በሥራ ላይ እያለሁ የመኖሪያ ቤቴ በመዉደሙ ጄቶቹ እኔን ለማደን የተላኩ መስሎ ተሰምቶኛል ።

ከሦስት ዓመታት አገልግሎት በኋላ ወደሞቃዲሾ ተቀየርኩ ።ከዚያም ቆርዬሌ በምትባል ከተማ ዉስጥ ተመድቤ ለስምንት ዓመታት ተቀመጥኩ ። በዚያም ኑሮዬ ትዳር መስርቼ የአምስት ልጆች አባት ለመሆን በቃሁ ።

በሶማሊያና በኢትዮጵያ መካከል የተደረገዉን ጦርነት ተከትሎ በርካታ ቁጥር ያላቸዉ ኢትዮጵያዉያን በስደት ወደ ሶማሊያ ገቡ ።የስደተኛ ካምፖችም በየቦታዉ ተቋቋሙ ። "ሕጻናት አድን ፌዴሬሽን" በሚባል አሜሪካዊ ምግባረ ሠናይ ድርጅት ዉስጥ በትርፍ ጊዜዬ በጀመርኩት ሥራ የኋላ ኋላ ቋሚ ሠራተኛ በመደረጌ ከመምህርነት ወደ ልማት ሠራተኛነት ተሸጋገርኩ ።ድርጅቱም በተለያዬ ጊዜ ወደ ዚምባብዌ ፤ ኬንያ ፤ህንድና ፊሊፒንስ ልኮኝ አጭርና ረዥም ሥልጠናና ትምህርት አግኝቻለሁ ።

### ሽገር ደርሶ መልስ

ዲሴምበር ዕሀየ፯ ላይ ከምሠራበት ድርጅት የምሥራቅ አፍሪካ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ጥሪ ተላለፈልኝ። ጥሪዉ ወደ አዲስ አበባ እንድሄድ በመሆኑ ፍጹም ዱብ ዕዳ ነበር ። ያ በርካታ ወንድም/ ጓዶቼን ኢሰብአዊ በሆነ መልኩ ያሳደደና የፈጀ የደርግ መንግሥት ሥልጣን ኮርቻ ላይ እንደተፈናጠጠ ነዉ ።ደም ደም አለኝ ።አገሬን ለማየት ከነበረኝ ከፍተኛ ጉጉት የማይተናነስ ፍርሃትና ስጋት ከበበኝ ። ቢሆንም አልቀረሁም ።አዲስ አበባ ገባሁ ።

ወደ አዲስ አበባ የመጣሁት ለአንድ ሳምንት ብቻ ለመቆየት ነበር ። በመመለሻዬ ቀናት ላይ ሞቃዲሾ በጎሳዎቿ መሃከል በተጀመረ ቁርቋሶ የዕልቂት አዉድማ በመሆኗ ሳቢያ ለሦስት ወራት ያህል መቆየት ግድ ሆነብኝ ።

የመጀመሪያዉ የአዲስ አበባ ቆይታዬ ፈጽሞ ሰላም አልነበረዉም ። ሞቃዲሾ ዉስጥ በተነሳዉ የርስ በርስ ጦርነት ሳቢያ እዚያ ያለዉ ቤተ ሰቤ ዕጣ ፈንታ ልቤን ያስጭንቀዋል ። ይብሱኑ ያስጨነቀኝ ደግሞ ከምሠራበት ድርጅት መ/ቤት ፊት ለፊት ግድግዳ ላይ በጉልህ ቀለምና በትላልቅ ፊደላት የተጻፈዉን "ሞት ለኢሕአፓ/" የሚለዉን መፈክር ማየቴ ነበር ። አሁንም የምታደን ፤ አሁንም የምፈለግ እየመሰለኝ ፈራሁ ።በዚሁ መነሾ በሦስት ወራት የዋቢ ሸበሌ ሆቴል ቆይታዬ አንዲት የአማርኛ ቃል ከአንደበቴ ሳይወጣ ዲዳ መስዬ ከረምኩ ።

ቤተሰቦቼን ለማግኘት ወደ ነጌሌ ስልክ ደዉዬ ወላጅ አባቴን አነጋገርኩት ። በሕጋዊዉ ስሜ ሳይሆን በቤት መጠሪያዬ "አብድርቃድር ነኝ ፤"ብዬ ስለ ጤንነቱና ስለ ቤተሰቡ ሁኔታ ጠየቅኩት ።ላገኛቸዉ እንደምፈልግም ነግሬዉ የምገኝበትን አድራሻ ገለጽኩለት ።እርሱም በእሽታ ስልኩን ዘጋዉ ።የመምጫዉን ቀን በናፍቆት ስጠባበቅ ቆይቼ በርሱ ምትክ የመጡት የቤተሰባችን የቅርብ ወዳጅ የሆኑት ወ/ሮ ገሮ ሆነዉ አገኘኋቸዉ ። አባቴ የእኔን አዲስ አበባ መገኘት በህልሙም ሆነ በዉኑ ያልጠበቀዉ ነገር ነበርና የነገርኩትን ሁሉ ፈጽሞ አላመነበት ኖሯል ። እናም ከቤተ ሰባችን ጋር የቅርብ ትዉዉቅ ወደነበራቸዉ ወደእነ አብዱርቃድር ሐዋስ ቤት አምርቶ " ልጃችሁ አብድርቃድር ከአዲስ አበባ ስልክ ደዉሎ የጠበቀ ሰላምታ አቀረበልኝ ፤ መጥታችሁ እዩኝ ብሏል፤" ብሎ ነገራቸዉ ። ልጃቸዉ አብድርቃድር አሜሪካ ዉስጥ እንደሚኖር በዉል የሚያዉቁት ወ/ሮ ገሮ ናፍቆታቸዉን ለመወጣት አዲስ አበባ ድረስ መጥተዉ በልጃቸዉ ፈንታ እኔን ሲያገኙኝ ደንግጠዋል ። ሆኖም ወደ ነጌሌ ተመልሰዉ እዉነቱን በማስረዳታቸዉ ታናሽ ወንድሜ ሁሴን አብዱላሂ ወደ እኔ ተልኮ መጣ ። እንደልብ ለመጨዋወት እንዲመቸን ወንድሜን ይዤዉ ወደ መርካቶ ወጣሁ ።የዚያን ቀን ዉሎአችን ሳይጠገብ አለቀና ለበነጋታዉ ተቀጣጥረን ፤ወደማረፊያዉ ከሸኘሁት በኋላ ወደሆቴሌ ተመለስኩ ።በማግሥቱ ግን ብቅ አላለም ። በሁለተኛዉም በሦስተኛዉም ቀናት አልተገኘም ። ደነገጥኩ ። የት ብዬ ልፈልገዉ ? ጭንቀት በጭንቀት ላይ ተነባበረብኝ ።

በሰባተኛዉ ቀን መልዕክት ደረሰኝ ።ለካስ ከሰሞኑ አዲስ አበባ ከተማ ዉስጥ የብሔራዊ ዉትድርና አፈሳ ይካሄድ ነበርና የልብሱን ሻንጣ እንኳ ከተከራየዉ አልቤርጎ ሳያወጣ እግሬ አዉጪኝ ብሎ መመለሱን ጻፈልኝ ። በእጅጉ አዘንኩ ። ሀዘኔ ፤የናፍቆቴን ያህል ከወንድሜ ጋር ለመገናኘት ባለመቻሌ ብቻ አልነበረም ።ሀገሬ ከገባሁ አንስቶ የማስተዉላቸዉ ሁኔታዎች በሙሉ ዕረፍት የሚሰጡ አልነበሩም ።

በተለይ አንድ ቀን በሆቴሉ መዝናኛ ሥፍራ ተቀምጠን ሳለ አንድ ወጣት በፖሊስ ሲደበደብ ከርቀት ተመለከትን ። ልጁ ራሱን ለማዳን "ምን አደረግኩ ጋሼ ?" እያለ ቢለምነዉም ፖሊሱ ሊተወዉ ባለመፍቀዱ ከእጁ አፈትልኮ ሮጠ ። ፖሊሱም ተከተለዉ።

ልጁ በመኪኖች መሃከል ተሹለክልኮ መንገዱን ለማቋረጥ ጥቂት እንደቀረዉ፤ ፖሊሱ በአዉቶማቲክ ተኩስ አስቀረዉ ። የዚያ የሊጋ ወጣት አካል ጎዳናዉ ላይ ተዘረረ ፤ደሙም በአስፋልቱ ንጣፍ ላይ ተንጣለለ። የሚዘገንን ትዕይንት ነበር። የሆቴሉን የመዝናኛ መስተንግዶ ጥለን ወጣን ። መልስ ባላገኘለትም ጎሊናዬ በጥያቄዎች ይዋከብ ገባ ።

ወደ ገጽ **7** ዞሯል

ፍኖተ ህብረት የኢሕአፓ ድምፅ በየሳምንቱ
ቅዳሜ ከ2 እስከ 3 PM በ730am ላይ
በዲሲና አካባቢዉ የሚተላለፍ ሬዲዮ ነዉ::

በስልክ ቁጥር **202 291 4217** አዘጋጆችን ማግኘት ይቻላል

ከገጽ 1 የዞረ

**ኮፈሌዎች በጾም ቀን እንዲሁም አዲስ አበቦች በጾም ፍቺ ቀን በደም ታጠቡ! ተቃውሞው በሀገርም በውጪም ተቀጣጥሎ ከርሞል::**

ሁለት ዓመት ያስቆጠረው የኢትዮጵያውያን ሙሲሊሞች ፍትሃዊ ትግል የወያኔን መሠረት እያነቃነቀ ባለበት በኮፈሌ በርካታ ሰዎች የታዘለች ህጻንን ጨምሮ በፌደራልና በአጋዚ ጦር አባሎች ህይወታቸው የተቀጠፈ ሲሆን ከአራት ቀን በኋላ የዋለው የረመዳን ጾም ፍቺ ደግሞ በአዲስ አበባ በሺዎች በብረት የተተለተሉበትና ርጉዝዋን ጨምሮ የበርካታ ሰዎችን ህይወት የበላበት ቀን ሆኗል። በሺ የሚቆጠሩ ሰላማዊ ዜጎችም እስከዛሬ በእስር ይሰቃያሉ። ይህን አስመልክቶ በዋሽንግተን ዲሲ የሚገኙ የሰልፍ ግብረ ኀይሎች እንዲሁም የዋሽንግተን ዲሲ ድምጻችን ይሰማ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ 3 ታላቅ ሰላማዊ ሰልፎ አካሂደዋል።

**የቻይና ኩባንያዎች ''ግንባታ'' ሀገረቷን ኪሳራ ላይ እየጣላት ነው**

የቻይና ኩባንያዎች በአሁኑ ሰዓት በመላ ሀገሪቱ በመንገድ ስራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ቢሆኑም የስራቸው ጥራት እጅግ የወረደ በመሆኑ የሀገር ሀብት እና የህዝብ ገንዘብ እየባከነ እንደሚገኝ ታውቆዋል::

በአዲስ አበባ ቀላል የባቡር መስመር ዝርጋታ ስራ ላይ የተሰማሩት የቻይና ኩባንያዎች ስራውን በአጭር ግዜ ይጨርሳሉ ተብሎ በወያኔ በኩል ሰፊ ቅስቀሳ ሲደገረግላቸው የነበረ ቢሆንም እስከ አሁን ድረስ ይሄ ነው የሚባል ትርጉም ያለው ስራ ሰርተው ባለማሳየታቸው ሕዝቡ በእጅጉ እየተበሳጨ መሆኑ በዚሁ የቀላል የባቡር መስመር ዝርጋታ ስራ ላይ የከተማዋን መንገዶች ሙሉ በሙሉ አፍርሰው በመቆፈራቸው ዜጎች በየቀኑ ጉድጉዋድ ውስጥ እየወደቁና እየሞቱ መሆናቸው እየታወቀ የወያኔ ባለስልጣናት፤ ቻይናዎቹ የህዝብን ሀብት ሲያባክኑ በዝምታ ማየታቸው በህዝቡ ዘንድ ከፋኛ ንዴት እየጫረ መሆኑ ታውቆዋል::

ከጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን እና በማዘጋጃው መሀከል ተቆፍሮ የነበረው የባቡር መስመር በግዴለሽነት እና በምንቸገረኝነት ስሜት በመሰራቱ በሚሊዮን ብር ወጪ የተደረገበት ስራ መልሶ መፍረሱ ታይቷል:: ከስድስት ወር በፊት የተጀመረው ይሄው ቁፋሮ እስከ አሁን መጠናቀቅ ሲገባው የተሰራው እንደገና በመፍረሱ እንደ አዲስ እየተቆፈረ ከመሆኑም በላይ የሀገሪቱ ሀብት እንደ አልባሌ እየባከነ ሲሆን የወያኔ ባለስልጣናት ከቻይናዎቹ ጋር በጥቅም የተሳሰሩ በመሆናቸው በዝምታ ማለፋቸው ታውቋል።

# ነጻ ሀሳብ

**የተቀነባበረ የወያኔ ሴራ በኢሕአፓ ላይ**

**ከ ግ.ተ**

**በዋሽንግተን ዲሲ የኢሕአፓ አባል**

የዛሬ አምስት አመት ገደማ በኢሕአፓ ውስጥ አንጃ የፈጠረው ቡድን ዴ የሚል ቅጽል ለጥፎ "ኢሕአፓ ዴ" የሚለውን የውርዴ ስም ይዞ ሲወጣ ኢሕአፓን የሚጠሉ ቡድኖችና ግለሰቦች በደስታ ተውጠው ከበሮ ሲደልቁ እንደነበር እናስታውሳለን። አንዳንዶቹ "ኢሕአፓ አለቀለት፤ ተሰነጣጠቀ፤ ጉድጓድ ውስጥ ገባ፤ ሞተ ተቀበረ ወዘተ... ስለዚህም ደስ ይበለን" የሚለውን የሞኝ ጩኸት በየአቅጣጫው እያሰሙ ለአንድ ሰሞን ሻምፓኝ ሲያጋጩ የነበሩ ሲሆን ሌሎች ደግሞ " እንዳሻን ለመቆጣጠርና ለመንዳት የምንችለው ኢሕአፓ በአዲስ መልክ ስለመጣ ይህንን በመደገፍና በማጠናከር ዋናውን ኢሕአፓን እናዳክም እናኮስስ" ብለው ተንቀሳቀሱ ። ለረዥም አመታት እንኳን የኢሕአፓን መግለጫ ይቅርና በውስጣቸው በእግረመንገድ የኢሕአፓን ጥሩ ተግባር በጥቂት ቃላት የሚጠቅሱትን መጣጥፎች እንኳ ማውጣት የሚተናነቃቸው ድረ ገጾች ይህን የአንጃ ቡድን ከማስተዋወቅ ጀምሮ መግለጫዎችን በተከታታይ ማውጣት ተያያዙት። በወያኔ የሚረዱ ራዲዮ ጣቢያዎች በአንድ ስሞን ብቅ ብሎ የነበረው የቴሌቪዥን ጣቢያ ሳይቀር የአንጃ መሪዎችን በተከታታይ በማቅረብ ቃለ ምልልስ አደረጉላቸው። ውሸትና ውዥንብርም በኢሕአፓ ላይ እንዲነዙ መድረክ ሰጧቸው። በሕዝብ ተቀባይነት እንዲያገኙ ልዩ አድርገው አቀርቧቸው። ጣሪያ እያጨሁ ቀሰቀሱላቸው። ይህ ሁሉ ኢሕአፓን ለማዳከም የተጠነሰሰና የተቀነባበረ ሴራ ነበር። ኢሕአፓ ግን ወይ ፍንክች የአባ ቢላዋ ልጅ ብሎ ተጠናክሮ ትግሉን ቀጠለ። አንጃውም ጥቂት ሳይቆይ አንዱን አንዱን እያወገዘ ተከፋፍሎ ለወሬ ነጋሪ እፍኝ የማይሞሉትን ብቻ ይዞ ቀረ።

አሁን ደግሞ ሰሞኑን ሌላ ከበሮ እየተደለቀ ይገኛል። ኢላማው ያው ኢሕአፓን ማዳከም ሲሆን ከበሮ ደላቂዎቹና አስደላቂዎቹ ለየት ይላሉ። በዲሲፕሊንና በስነምግባር ጉድለት ፓርቲው ያባረራቸውና ድርጅታዊ ግዴታቸውን መወጣት አቅቷቸው ራሳቸውን ከድርጅቱ ያገለሉ ግለስቦች ናቸው የሰሞኑ ተዋንያኖች። እነዚህ ግለሰቦች እንኳን ታጋይ ድርጅት የሚጠያቃቸው መሠረታዊ የዲስፕሊንና ብቃት ሊያሟሉ ይቅርና በግል ህይወታቸው አነስተኛ ስነምግባር የሌላቸው ናቸው። ማንና ምን መሆናቸውንም ማወቅም ስለማይችሉ ለራሳቸው ትልቅ ግምት በመስጠት ድርጅቱ እኛ ነን ስለሆነም እነእከሌን አባረናል፤ ጉባዔ እናደርጋለን፤ አመራር እንመድባለን ወዘተ... በማለት ነገ የሚጋለጡበትንና የሚያፍሩበትን የውዥንብር ጋጋታ ሲያሰሙ ሰንብተዋል። ጸረ ድርጅት የሆኑ የቅስቀሳ በራሪዎች ለማሰራጨት ሞክረዋል። ካለፈው የተለየ ቢኖር የሁኔታውን እውነተኛነት በመገምገም ብዙዎቹ ድረገጾች ለዚህ ተባባሪ ላለመሆን መወሰናቸው ነው። አንዳንዶቹም ተሳስተው ለጥቂት ሰዓታት ያወጡ ቢኖሩም መሳሳታቸውን አውቀው ወዲያውኑ የእርምት ርምጃ ሲወስዱ ታይተዋል። አንዳንድ ጠርቀም ያለ ገንዘብ ከወያኔ ያገኛሉ እየተባሉ የሚታሙ ራዲዮኖችና በሀገር ቤትም በረከት ስምኦን በጀርባ መሰረተው የሚባል አንድ መጽሄት ግን ተባባሪ በመሆን የእነዚህን አፍራሽ ግለስቦች ቅስቀሳ እያጋነኑ ሲያሰራጩ ሰንብተዋል።

ብዙ ሰዎች የዛሬ አምስት አመት አንጃው በኢሕአፓ ላይ የወሰደው እኩይ ተግባር ሆነ አሁን ደግሞ እፍኝ በማይሞሉ ግለሰቦች እየተወሰደ ያለው አፍራሽ ሙከራ ይገርማቸዋል። አንዳንዶች ከግለሰቦች አለመጣጣም ወይም ከአንዳንዶች ብልሹ ባህሪ የመጣ ይመስላቸዋል። እኔ ግን በኢሕአፓ አባልነቴ ሁለቱንም ሁኔታ በቅርብ ተከታትዬ እንዳየሁትና እንደታዘብኩት የወያኔ የረቀቀ ተንኮልና ስልት ሳይሆን አይቀርም የሚል ጠንካራ መደምደሚያ ላይ ደርሻለሁ። ወደዚህ መደምደሚያ ላይ ለመድረስ ምክንያት የሚሆኑ ብዙ ማስረጃዎች አሉኝ።

ከአንጃው ልጀምር። የአንጃውን መሪ ተከትለው ከሄዱት ውስጥ ብዙዎቹ በቅንነት ወይም በመታለል የሄዱ መሆናቸውን አልጠራጠርም። የአንጃው መሪና አንዳንድ ተከታዮቹ ግን ከወያኔ ጋር ግንኙነት አልነበራቸውም ለማለት አይቻልም። ብዙ ወደዚህ መደምደሚያ ሊያደርሱ የሚችሉ ጉዳዮች አሉና። በመጀመሪያ ደረጃ አንጃ ፈጥሮ ከኢሕአፓ ለመነጠል ምክንያት የሆነው ለወያኔ ፈርመን አገር ቤት ገብተን እንቀሳቀስ በሚል ይገፋ የነበረው አቋም ተቀባይነት በማጣቱ ምክንያት መሆኑ ግልጽ ነው። ማናቸውንም አቋም ይዞ ሌላውን ለማሳመን መሞከርና መከራከር ሙብትም ዴሞክራሲያዊ አሰራርም ሲሆን የአብዛኛውን አባል ውሳኔ ላለመቀበል ሲባል አንጃ ፈጥሮ ድርጅትን ለማፍረስ መጣር ግን ከኋላ ምን አለ የሚለውን ጥርጣሬ ያስከትላል። የአንጃው መሪ ከአላሙዲን ሰዎች ጋር ግንኙነት እንደነበረው ብዙ ሰዎች የሚናገሩት ሲሆን የቅርብ ተከታዮቹ ከሆኑት መካከል አንዱ ደግሞ ከቀንደኞቹ የወያኔ የጸጥታው ሹም ከጌታቸው አሰፋ ጋር የቆየ ግንኙነትና ጓደኝነት እንደነበረው ራሱም የሚክደው አይደለም። ስም መዘርዘሩ አስፈላጊ ባይሆንም ሌሎቹም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከወያኔ ጋር ግንኙነት ያላቸው መሆኑ የታወቀ ነው።

ወደ አሁኖቹ አፍራሽ ግለሰቦች ስንመጣ ደግሞ ከወያኔ ጋር ያላቸው ትሥሥር ግልጽ ይሆንልናል። ከእነዚህ መካከል አንዳንዶቹ ከበረከት ስምኦን ጋር አብሮ አደግና ጓደኛ እንደነበሩ ሲነገር የቆየ ነው። በአንድ ወቅትም በረከት ስምኦን ወደዋሽንግተን መጥቶ በነበረበት ወቅት ተገናኝተው የተጫወቱ መሆናቸውም ይታወቃል። በጁላይ መጨረሻም የበረከት ስምኦን ጓደኛና ልዩ መልእክተኛ ታደሰ ጥንቅሹ ወደዋሽንገተን መጥቶ በነበረበት ሰዓት አንዳንዶቹን ፈልጎ እንዳገኘና እንደተጫወቱም ተወርቷል።

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ከገጽ 5 የዞረ

ወጣቱ ትዉልድ እስከመቼ ድረስ ይተኮስበት ይሆን?...ኢትዮጵያስ ዉስጥ ሁሉም ነገር በኃይልና በግዳጅ የሚፈጸመዉ እስከመቼ ይሆን??...

## ሞቃዲሾ .....የነበረዉ እንዳልነበረ፤

በዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል አዉሮፕላን ከአዲስ አበባ ሞቃዲሾ ገባሁ ።ሁሉም ነገር እንዳልነበር ሆኖ ጠበቀኝ ።የከተማይቱ ሕንጻዎች ሙሉ በሙሉ፤ ወይም በከፊል ወድመዋል ።ጣራዎች ተደርምሰዋል ፤ግድግዳዎች ተነድለዋል።የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ ኬብሎች ተበጣጥሰዉ ምሰሶዎቻቸዉ ተገንድሰዋል ።የተቃጠሉ መኪናዎች በየመንገዱ ዳር ከስለዉ ተገትረዋል ።የጠለሸ ዳመና ከሰማይ ተንጠልጥሎ ይታያል። የአዉራ መንገዱ ዳርና ዳር የመቃብር ሥፍራ ሆኗል ።በታሪኩ ፤በባህሉ ፤ በኃይማኖቱና በቋንቋዉ እንደ አንድ ቤተሰብ ይታይ የነበረዉ ሕዝብ እርስ በርሱ በመቆራቆሱ ለማመን እስኪያዳግት ድረስ ሶማሊያ ዉስጥ ሕይወት ነጥፏል ።በከተማዉ ዉስጥ የማዉቃቸዉ ሰዎች አብዛኛዎቹ የጎሳዉ ጦርነት ሰለባ መሆናቸዉን ከአዉሮፕላን ማረፊያዉ ሜዳ የተቀበለኝ ጓደኛዬ አረዳኝ።

በማግሥቱ፤ ተሚጣ ባለቀች ተስፋ ምናልባት ቤተሰቦቼን ባገኝ በማለት ወደ ቆርዬሌ አመራሁ ። በየመንገዱ ዳር በሙቶ የሚቆጠሩ ሬሣዎች ወድቀዉ በማየቴ ዘገነነኝ ።ስሜቴን መቆጣጠር አቃተኝ ፤ አነባሁም ። ከዐይኖቼ ፊት የተዘረጋዉ ምድር ሁሉ መቃብር ሆኗል ።አንድ ዘመናዊ ት/ቤት በከባድ መሣሪያ ድምጥማጡ ጠፍቶ የድንጋይ ቁልል ሆኗል ። ዐይኖቼ የዉድመቱን ቅሪት ሲያሳዩኝ ህሊናዬ ደግሞ ተቆራርጠዉና ተበጣጥሰዉ ለዘለዓለሙ ያንቀላፉ ሕጻናትን ቀርጾ አመለከተኝ ።አፌ ተለጉሞ፤ ዐይኖቼ እንባ ሲያጎርፉ ሁለመናዬ ከምድር ወደሰማይ በምሬት ይጮሃል ።

ሁኔታዉ በሙሉ የትዳር ጓደኛዬንና የልጆቼን ዕጣ ፈንታ ከወዲሁ የሚያመላክት ነበር ።ይሁን እንጂ ወደቤቴ ሄጄ በፍርስራሹ ዉስጥ እንኳ የሥጋቸዉንና የአጥንታቸዉን ቅሪት በእንባ ተሰናብቼ ለመመለስ አቅጄ የጭንቅ ጉዞዬን ተያያዝኩት።...የቤቴ ግድግዳና ጣራ በጥይት ተደብድቧል ።ደረቴ ዉስጥ ከሚንደፋደፈዉ የልቤ ምት ጋር እየታገልኩ፤ ወደ ዉስጥ ዘለቅሁ ። የጸጥታዉ ጩኸት ሞት በግዝፈት መንገሱን ይነግረኛል። ድምጼን አሰባስቤ ተጣራሁ ። ባለቤቴ ብቅ አለች ። ላዉቃት እስኪሳነኝ ድረስ ተጎሰቋቁላለች ። ልጆቼም " አባ...አባ....." እያሉ ተሯሩጠዉ መጡ ። ተቃቅፈን ተላቀስን፡፡

**(ይቀጥላል)**

## ከኢሕአፓ ጋር ለሚደረጉ ግንኙነቶች የሚከተሉትን መጠቀም ይቻላል

ስልክ **202 291 4217**
ኢሜል **espic@aol.com**
ፓስታ **eprp**
**P.O.Box 73337**
**Washington Dc 20056**
ድረ ገጽ **eprp.com**
ፍኖተ ዴሞክራሲን ለማዳመጥ **Finote.org**

ከገጽ 6 የዞረ

### የተቀነባበረ የወያኔ

ሌሎችም በወያኔ ጸጥታ ክፍል ውስጥ የሚሰሩ ዘመዶችም እንዳሏቸው ቅርብ ለሆኑ ጓደኞቻቸው መናገራቸው ይታወቃል። እነዚህ ግለሰቦች ድርጅቱ ውስጥ በነበሩ ጊዜ ስራዎች እንዳይሰሩ ዘወትር እንቅፋት ሲፈጥሩ እንደነበር፤ አዳዲስ አባላት ድርጅቱን እንዳይቀላቀሉ፤ ያሉትም እንዲወጡ፤ አልፎ ተርፎም ደጋፊዎች እንዳይሰባሰቡና የተሰበቡትም እንዲበተኑ፤ ሲቀሰቅሱና ሲገፋፉ እንደነበር እኛ በዋሽንግተንና አካባቢው የምንገኝ የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች የምናውቀው ነው። በነዚህ ግለሰቦች የተቀሰቀሱ አባላትና ደጋፊዎች ይህን ጽሁፍ ሲያነቡ እውነቱን ለማረጋገጥ ድምጻቸውን እንደሚያሰሙ ተስፋ አለኝ። እነዚህ አፍራሽ ግለሰቦች በተግባር ሲያከናውኑ የነበሩትና አሁን ደግሞ በይፋ በኢሕአፓ ላይ የጀመሩት ዘመቻ ከላይ ከተጠቀሰው ታሪካቸው ጋር ተዛምዶ ሲገመገም የወያኔ መልእክተኞች መሆናቸውን ያረጋግጥልኛል።

ቅስቀሳቸውን የሚያራምዱላቸው መገናኛ ብዙሀን አብዛኞቹ ከወያኔ ጋር የተነካኩ መሆናቸው ሲታወቅ ደግሞ ጥርጣሬዬን የተሟላ ያደርገዋል። በዋሽንግተን ዲሲ ለሁለት ሳምንት መድረክ ስጥቶ ሲያስተናግድላቸው የነበረው ራዲዮ ባለቤት እሱ በተደጋጋሚ ቢክድም በሚስቱ ስም ትልቅ ህንጻ አገር ውስጥ መስራቱና በአንድ ወቅት ወያኔ ግብር አልከፈለም ብሎ ቤቱን በመያዣ ስም መያዙ አገር ያወቀው ጸሐይ የሞቀው ወሬ ነው። ሰሞኑን ደግሞ ወያኔ የዚህን ራዲዮ ባለቤት አንዳንድ ተግባሮች ካከናውንክ ቤቱን እንለቅልሃለን ብሎ ቃል እንደሰጠው ይወራል። የዚህ ራዲዮ አዘጋጅ ለአፍራሾች መድረክ በመስጠት ያካሄደው ቃለ ምልልስ የወያኔን ተልእኮን ለማሟላት የተደረገ ይሆን? አንዳንድ የሚጠራጠሩ የዋሆች ቢኖሩም እኔ ነው እላለሁ። ይህ ግለሰብ በፕሮግራሙ መግቢያ ላይ የኢሕአፓ ደጋፊ ለኢሕአፓ አዛኝ መስሎ ያሰማው የአዛኝ ቅቤ አንጓች እንጉርጉሮው ማንንም ሊያታልል አይገባም።ግለሰቡ ምን ጊዜም የኢሕአፓ ደጋፊ ሆኖ አያውቅም። እኛ አባላቶቹ ደግሞ የኢሕአፓ ደጋፊ ሆኖ እንደማያውቅ እናውቃለን። እስኪ መች ነው የኢሕአፓን መግለጫ አንብቦ የሚያውቀው። ትናንት ተፈጠሩ የተባሉትን ድርጅቶች በነጋ በነጋ ሲያስተዋውቅ፤ ዛሬ ጸረ ኢትዮጵያ አቋማቸው ለተጋለጠባቸው፤ ለእነ ጁሃር መሀመድ በተደጋጋሚ መድረክ ሲሰጥ ከአንጃው እንቅስቃሴ በስተቀር ስለ፤ኢሕአፓ ተናግሮ ያውቃል? ኢሕአፓ 39ኛ ዓመቱን ባከበረበት ወቅት ከአንድ የአመራር አባል ጋር ቃለ ምልልስ ሲያደርግ ሰምቻለሁ። በብዙ አመት ውስጥ አንድ ጊዜ ማለት ነው። ከዚህ ውጭ ግን አልሰማሁም። እኔ ግን ይኸው ከ20 ዓመት በላይ የኢሕአፓ አባል ሆኜ በአካባቢው እገኛለሁ፤ አንድ ቀንም ቢሮ አይቸው አላውቅም፤ ወይም መጥቶ ነበር የሚል አልሰማሁም። ይህን ያለው ለማምታት ነው። ዘርጋው የተባለውን ግለሰብ የአመራር አባል ነው የደመደምበትና በኋላ እጅ ከፍንጅ ሲያዝ በስልት ያስተባበለበት ሁኔታ ሲገመገም አላማው ምን እንደሆነ ያሳያል። በዚያን ቀን በራዲዮ ፕሮግራሙ መግቢያ ላይ ለኢሕአፓ የሚቆረቆር መስሎ ያሰማው እንቶ ፈንቶም ተአማኒነት አግኝቶ በፕሮግራሙ የሚረጨው መርዝ ተቀባይነት እንዲያገኝ ነው እንጅ ከልቡ አለመሆኑ ግልጽ ነው።

በነገራችን ላይ ይች ተአማኒነት ለማግኘት የምትደረግ ታክቲክ የወያኔ ናት። በዚህ አካባቢ አንዳንድ ራዲዮ ጣቢያዎች " ወያኔ ጠላት ነው፤ ወያኔ መወገድ አለበት፤ ወያኔን መታገል አለብን" አለብን"…. ወዘተ... የሚሉትን ባዶ ቃላት እስከ ሰማያ ሰመያት የሚያጮሁት ተዓማኒነት ለማግኘት ነው። እነዚህን ቃላት እያጮሁ በፕሮግራማቸው ግን ድርጅቶችን የሚያዳክሙ፤ ሰውን እርስ በርስ የሚከፋፍሉ፤ ትግሉን የሚጎትቱ መርዝ ለበስ ፕሮፓጋንዳዎችን በማሰራጨት ወያኔ ይጠቅማሉ።

እነዚህ የወያኔ አገልጋዮችና ተገዥዎች ናቸው እንጅ የወያኔ ጠላቶች ናቸው ብሎ መድምደም አይቻልም። እስቲ ነገሩን ጠለቅ ብለን እንየው ። ጠይቄ እንደተረዳሁት በዋሽንገተን አካባቢ አነስተኛ ዋጋ ያለው የአንድ ሰዓት የራዲዮ ፕሮግራም በወር 1600 እስከ 2000 ዶላር ያስወጣል። አንዳንዶቹ በሳምንት የሁለት ሰዓት ፕሮግራም አላቸው አንዳንዶቹ 4 ሰዓት ። የሁለት ሰዓት ፕሮግራም ያላቸው በወር ከ3200 እስከ 4000 (በዓመት ከ38000 እስከ 48000) ብር ወጭ ሲያደርጉ አራት ሰዓት ፕሮግራም ያላቸው ደግሞ በወር ከ 6400 እስከ 8000 ( በዓመት ከ76800 እስከ 96000) ያወጣሉ። አንድ በታክሲ ስራ ላይ የተሰማራ፤ ቤተሰብ ያለውና ከተደራጀ ሃይል ወይም ከአባላት መዋጮ ገንዘብ የማያገኝ ግለሰብ ይህንን ሁሉ ገንዘብ እየከፈለ እንዴት ራዲዮኖችን ማካሄድ ይችላል ለሚለው ጥያቄ መልሱን ለአንባብያን እተዋለሁ። ለኔ ግን ግልጽ ነው። አንድ ወዳጄ ወያኔ በአሜሪካ በተለያዩ ስቴቶች የሚገኙ ራዲዮኖችን እንደሚቆጣጠር ነግሮኛል። አንዳንዶቹ የወያኔ ፕሮግራሞች ብቻ የሚያካሄዱ በግልጽ ፋይናንስ የሚያደርጋቸውና የሚቆጣጠራቸው ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ ፋይናንስ እያደረገ ተቃዋሚውን ለመከፋፈል ሴራውን የሚረጭበት ነው። በወያኔ ፋይናንስ የሚደረጉ በግልጽ የወያኔ ፖሊሲ የሚደግፉ ግን ገለልተኛ ነን ማለት የሚቃታቸው እንደ አገር ፍቅርና አንድ ኢትዮጵያ ዓይነቶች ሲሆን የመጨረሻዎቹ ደግሞ ወያኔን እስከ መጨረሻው እያወገዙ በረቀቀ ዘዴ ወያኔ የሚፈልገውን የከፋፋይነትና ታጋዮችን የማዳከም ተግባር የሚያከናውኑ ናቸው። ያለፉት 20 ዓመታት ታሪካችን የሚያሳየን ይህንኑ ነው። አሁን ግን ካለፈው ተምረናል። አንታለልም።

የወያኔ ተላላኪዎች የሆኑት የአንጃው ሰዎችና በቅርብ በኢሕአፓ ላይ የስም ማጥፋት ዘመቻ በማካሄድ እየተንቀሳቀሱ ያሉት አፍራሽ ግለስቦች በአንድ ላይ መስራት ጀምረዋል። የአንጃው መሪ በየቦታው የአፍራሾቹን ስም እያወደሰ በአንዳንድ ስቴቶች የሚገኙትን ራዲዮ ጣቢያዎች በመቅረብ መድረክ እንዲሰጧቸው ቅስቀሳ አካሂዷል። በአንዳንድ አካባቢውም የአፍራሾችን የቅስቀሳ ወረቀት በመበተን ከመተባበር ጀምሮ የመገናኛ አውታሮችን (ለምሳሌ አትላንታ) እንዲያገኙ የአንጃው ሰዎች አመቻችተውላቸዋል።

ይህን የተቀነባበረ ዘመቻ ወያኔም በሀገር ቤት እያስተጋባው ይገኛል። ሎሚ የሚባለው በረከት ስምኦን አቋቋመው የሚባለው መጽሔት ኢሕአፓ እነ እገሌና እነ እገሌ የተባሉትን አመራር አባላት አባረረ፤ አሰናበተ ወዘተ... በሚል በሬ ወለደ ቱልቱላውን ሲነዛ ቆይቷል። ሌሎችም የወያኔ ሚዲያዎች እየተቀባበሉ እንደሚያናፋት ይጠበቃል።

ከላይ እንዳልነው ወያኔ በኢሕአፓና በሌሎች ታጋይ ድርጅቶች ላይ የተቀነባበረ ዘመቻውን አጠናክሮ በመቀጠል ላይ ይገኛል። ያለ የሌለ አገልጋዮችን አሰልፏል። በእኛ በአባላቱና በደጋፊዎቹ በኩል ከመቸውም የበለጠ ግልጽነት አለን። በሕዝቡም ዘንድ ካለፈው በተሻለ መንገድ ግልጽነት እንዳለ ይታያል። ዝምብ ቢሰበሰብ ወስከንባይ አይከፍትም ነውና እንዳለፉት ጊዜያት ሁሉ ወያኔ አገልጋዮችን በማስተባበር በረቀቀ ዘዴ የቃጣብንን ሴራ በተባበረ ክንድ ደቁሰን እንደምናከሽፈው ምንም ጥርጥር የለንም።

# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
# Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

EPRP
PO Box 73337
Washington DC. 20056
Tel: 202 291 4217 Fax: 202 291 7646

E mail: espic@aol.com
Web site: www.eprp.com

EPRP
BP 22
Bois Colombes
France


ሐምሌ 29 ቀን 2005 ዓ.ም.

## በሙስሊም ወገኖቻችን ላይ ወያኔ ያካሄደውን ጭፍጨፋ ኢሕአፓ ያወግዛል

ባለፈው ቅዳሜ ሐምሌ 26 ቀን የወያኔ ወታደሮች በሙስሊም ዜጎቻችን ላይ ያካሄዱትን የጅምላ ግድያ ኢሕአፓ በጥብቅ እያወገዘ ወንጀሉን ያዘዙትና ድርጊቱን የፈጸሙትም ባስቸኳይ ለፍርድ እንዲቀርቡ ይጠይቃል። በግፍ የታሰሩባቸው የሃይማኖት አባቶች (ኢማሞች) እንደፈቱላቸው ከዋቤ ከተማ ወደኮፈሌ ሲጓዙ በነበሩ ሰላማዊ ሰዎች ላይ የወያኔ ወታደሮች አረመኔያዊ በሆነ ሁኔታ የእሩምታ ተኩስ ከፍተው አንድ ህጻንን ጨምሮ በርካታ ዜጎቻችን የገደሉ ሲሆን በሙቶ የሚቆጠሩ ሰዎችን ያቆሰሉ መሆናቸው ታውቋል። በሻሸመኔና በሌሎች ከተሞች በድርጊቱ ተበሳጭተው ሰላማዊ ተቃውሞ ያደርጉ በነበሩ ወገኖች ላይም የወያኔ ወታደሮች ተኩስ ከፍተው በርካታ ሰዎችን የገደሉ መሆናቸው ታውቋል። ባጠቃላይ በሁሉም ቦታዎች ከ 25 በላይ የሚሆኑ ወገኖቻችን መገደላቸው እንዲሁም የቆሰሉት ሆስፒታል የገቡ መሆናቸውና ሌሎች በሺ የሚቆጠሩ ተይዘው እስር ቤቶች ውስጥ የተወረውሩ መሆናቸው ታውቋል።

የወያኔ አምባገነን አገዛዝ የተመሰረተውም ሆነ ህይወት አግኝቶ ተጠናክሮ እየቀጠለ ያለው ወገኖቻችንን በመግደልና በመጨፍጨፍ መሆኑን ያለፉት 21 የግፍ ዘመናት አሳይተውናል። የሕግ የበላይነትን ማስጠበቅ፤ የዜጎችን መብት ማክበር ፤ ሰላማዊ ለሆኑ ሕዝባዊ ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ መመለስ ወዘተ… በአምባገነኑና ዘረኛው አገዛዝ የሚታወቁ አይደለም። ወያኔ የሚያውቀው ቋንቋ፤ ግድያ እስራት ጭፍጨፋ ነው። ስለዚህም ነው 18 ወራትን ያስቆጠረው የሙስሊሙ ኅብረተሰብ በሰላማዊ መንገድ ለጠየቀው ጥያቄ መሪዎችን ጨምሮ በርካታ ሙስሊሞችን በማሰርና ንጹህ ዜጎችን በመግደልና በመጨፍጨፍ ወያኔያዊ መልስ እየተሰጠ ያለው።

የሰሞኑ የወያኔ አገዛዝ አረመኔያዊ ድርጊት በጽኑ መወገዝ ያለበት ቢሆንም ድርጊቱን በማወገዝና ተቃውሞን በማሰማት ብቻ የወያኔ አረመኔያዊና ጸረ ሕዝብ ጭፍጨፋ ማስቆም አይቻልም። የሕዝብን ስቃይና በደል ለአንዴም ለሁሌም ማስቆም የሚቻለው ሁለገብ በሆነ መንገድ ታግሎ አገዛዙን ከስልጣን ማስወገድ ሲቻል ስለሆነ የአገር ፍቅር የሚሰማው ዜጋ ሁሉ ኃይሉን አስተባብሮ በአረመኔው አገዛዝ ላይ ጥቃት እንዲሰነዝር እንደወትሮው አሁንም ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

የወያኔን አምባገነን አገዛዝ በተባበረ ትግል እናስወግድ
ኢሕአፓ

### አይ አዲስ አዲስ አበባ

ዲያቢሎስ ጽዋ ሲጐነጭ በቤተ መንግስትሽ
አጋንንት በመንበረ ፓትርያርክ ሲሿሿሙብሽ
ጂኒ ሲጫን በመስጊድሽ
ተኮፍሶ ሲብነሸነሽ
ዝቅ አድርጎ ሲያራክስሽ
ምን አገኘሽ ዝም ማለትሽ
እኔ ሳውቅሽ ህያው ነበርሽ
በልጆችሽ የተከበርሽ አንድነትን የተሻማሽ
በምብ ጥለሽ ግራዚያኒን ያባነንሽ
ፋሽስት ደርጉን ያተራመሽ ባንዳውን የቆላሽ
ጥለሽ ወድቀሽ መስዋትነትን ያከበርሽ፤ ያሳየሽ
ምነዋ የትናንት ህያው ዛሬ በደንሽ
ጀግና ወላጅ ማህጸን አጣሽ?
ምን ታደርጊ ምሁርሽ በሞራ ተሞልቶ
ሆደ አምላኩ ቀፈታም እንደስልቻ ለፍቶ
ቁስ ሼኩ የሀይማኖት አምላኩን ዘንግቶ
የሀገሩን ታሪክ ክዶ አውቆ ረስቶ
ሕዝቡን ንቆ ቅጥረ ነጭ ሙንጣዝ ፈልቶ
ደም መጣጭ ቅጥረኛ ትኳን ፈልቶ ተንሰራፍቶ
አህያዋ ን ሆኖ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል በልቶ
ተንቀጥቅቶ ለጠላቶቹ አድሮ ጀሮ ጠብቶ
በሄደበት ሸኚ ዳይፐር አጥላቂ በዝቶ
ሰው መሳይ በሸንን ሙቃሙቅ በየመድረኩ ጭቶ
ሳይጠሩት አቤት ሳይልኩት ወዴት መጫኛ አጋሰስ በዝቶ
ሁሉም ነቅዞ እንደ ሥጋ ተልቶ
እንዲባል ግም ለግም አብሮ አዝግም
ወስኛለሁ ተማሪ ሆኜ በሱ አልማርም
መማር ማስተማሩንም እኔው ልሸከም
ካለፉት ተማሪዎች አስተማሪዎች ትምህርት ልቅሰም

አንተነህ ከቶሮንቶ